# ሜ/ጀ ፋንታ በላይ - (1928 – 1981) - ስድስተኛው የኢትዮጵያ አየር ኃይል አዛዥ

ምንጭ - የኢትዮጵያ አየር ኃይል ታሪክ (1921 – 1983)



ሜጀር ጀኔራል ፋንታ በላይ ከአባታቸው ከፊታውራሪ በላይ ወንዴና ከእናታቸው ከወ/ሮ ናፈቁ በለው በጐንደር ከ/ሃገር በሊቦ አውራጃ በለሳ ወረዳ በ1928 ዓም ተወለዱ ። የቤተሰቡ ሶስተኛ ልጅ የነበሩት እኒህ ጀግናና አዋቂ ጀኔራል መኰንን በጣልያን ወረራ ጊዜ ጀግንነታቸውን ካስመሰከሩ እናትና አባት የተወለዱ የቤተሰቡ ሶስተኛ ልጅ ናቸው ።

ሜ/ጀ ፋንታ በላይ ከአየር ኃይል አዛዥነታቸው ወደ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲዛወሩ በዚያን ወቅት "ተነሳ ተራመድ" የተባለው የአየር ኃይል መፄሄት አዘጋጅ ቃለ መጠይቅ አድርጐላቸው ከሰጡት ሰፋ ያለ ማብራሪያ የተገኘው መረጃ እንደሚያስረዳው እኒህ ብልህና አስተዋይ መኰንን ከልጅነት ጀምሮ አካባቢያቸው ከነበሩት ጓደኞቻቸው በትምህርትም ሆነ በምግባራቸው የላቁ እንደነበሩ ታውቋል ። ለአገራቸው ጀብዱ ሰርተው ላለፉት አባታቸው ውለታ ፣ ለልጃቸው ለፋንታ በላይ እንዲከፈል ሆኖ መድኃኔዓለም ት/ቤት በአዳሪ ተማሪነት በመግባት ከ 1ኛ እስከ 11ኛ ክፍል ድረስ ተምረዋል ። ከልጅነት እስከ ዕውቀት ድረስ ያሳዩት ትምህርት የመቀበል ችሎታ ከፍተኛ ስለነበረ በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ በየክፍሉ አንደኛ እየወጡ 6ኛ ክፍል መድረስ ችለዋል ። በአጠቃላይ እስከ 11ኛ ክፍል ያለውን ትምህርት በላቀ ውጤት በስድስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለመጨረስ በቅተዋል ።

ሜ/ጀ ፋንታ ያሳለፉትን የልጅነት ጊዜ በተመለከተ ለ"ተነሳ ተራመድ" መፅሄት በሰጡት ቃለ ምልልስ " ...... በውነቱ ከቤተሰባችን ውስጥ ጭምት የምባል እኔ ነበርኩ ።እንዲያም ሲባል ክልፍልፍና ቅብጥብጥ አልሁን እንጂ ቀልጣፋ ነበርኩ ። ጥቃትን ከልጅነቴ ጀምሮ አልወድም ። በጥልም ሆነ በጨዋታ አሸንፎ መግባትን እንጂ መሸነን አልፈቅድም ። ብዙውን ጊዜም ማሸነፍ ይሆንልኛል ። አዘውትረው ከነበረው ጨዋታ አንዱ የእግር ኳስ ነበር ። በአጠቃላይ በባሕሪይ በእድሜና በሥራ ልምድ ሂደት ከሚመጣ ዕድገት በስተቀር ብዙም ከበፊቱ የተለወጥኩ አይመስለኝም" ብለዋል ። ጀ/ል ፋንታ ከልጅነታቸው አብሯቸው የመጣ አየር ኃይል የመግባት ፍላጐት አልነበራቸውም ። ፍላጐቱ እያደጉና በትምህርት እየገፉ ሲሄዱ የመጣ ነው ። በተለይም ከእሳቸው በፊት የገቡትን አለባበስ ሲያዩ ፍላጐታቸው እየጨመረ መምጣቱ አልቀረም ። ሆኖም የመጀመሪያው ፍላጐታቸው ውጭ አገር ተምሮ ኢንጅነር መሆን ነበር ። አየር ኃይል ከገቡ በኋላ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ለኢንጅነሪንግ ትምህርት ወደ ውጭ የመላክ ዕድል እንዳለ በሰሙ ጊዜ ለመቀጠር ፈራ ተባ ይሉ የነበረው ቀርቶ ቁርጥ ያለ ውሳኔ አደረጉ ፡፡

በትምህርት በጣም ጐበዝ እነደሆኑ የሚያውቁት የመድሃኔአለም ት/ቤት አስተማሪዎቻቸውና የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ገና ልጅ ስለሆንክና በትምህርትህም በጣም ጐበዝ ስለሆንክ አስራ ሁለተኛን ክፍል እንደጨረስክ ወደ ውጭ የመላክ ዕድልህ በጣም ሰፊ ነው ፤ ስለዚህ አየር ኃይል አትግባ የሚል ምክር ቢሰጧቸውም አሻፈረኝ ብለው ገቡ ፡፡ ለአስተማሪዎቻቸው “ለማንኛውም ክረምቱን አሳልፌ እመለሳለሁ” ብለው ወደ ቢሾፍቱ አቀኑ ፡፡ በ1945 ዓም አየር ኃይል ተቀጠሩ ፡፡ አየር ኃይል ገብተው ለመጀመሪያው አንድ ዓመት ተኩል የሬድዮ መገናኛ ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ ወደ በረራ ትምህርት ቤት ተዛውረው ኢዚያም በቀለምና በበረራ ትምህርት አንደኛ በመሆን በትምህርት ቤቱ የክብር ዕውቅና ባህል መሰረት በርዕሰ ብሄሩ አማካኝነት የሚሰጠውን የፌሪ ትሮፊ ከፍተኛ ሽልማት አግኝተዋል ፡፡



አሜሪካን አገር የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በከፍተኛ ማዕረግ በአራት ዓመት ብቻ አገኙ ፡፡ ይህን ከፍተኛ ውጤት ያገኙት ለስታፍ መኰንንነት የአጭር ጊዜ ኰርስ ተልከው ኰርሱን በጥሩ ውጤት እንደጨረሱ ለከፍተኛ ትምህርት ዕድል እንዲሰጣቸው እዚያው አሜሪካን አገር ሆነው አየር ኃይልን ጠይቀው በሶስት ዓመት ጨርሰው እንዲመለሱ ተፈቅዶላቸው ነው ፡፡ መኰንኑ ትምህርታቸውን ሴንት ሉዊስ ዩኒቨርሲቲ በመቀጠል ከመደበኛ ፕሮግራሙ በላይ ኰርሶች እየወሰዱ ሶስት ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በኤሮኖቲካል አድሚኒስትሬሽን የመጀመሪያ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዲግሪያቸውን አገኙ ። በውጤታቸው የተደነቁት የዩኒቨርሲቲው አስተማሪዎች ለማስተማርስ ዲግሪ እንዲቀጥሉ አበረታትተዋቸው አየር ኃይልን እንደገና ጊዜ እንዲራዘምላቸው ጠየቁ ። የጠየቁት ግን የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ለመጨረስ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው በማስረዳት ቢሆንም ጥያቄውን ባቀረቡበት ጊዜ የማስተርስ ዲግሪ ተፈላጊ ኰርሶችን በመውሰድ ትምህርታቸውን በትጋት ቀጥለው ብዙ ገፍተው ነበር ። አየር ኃይሉም ጒበዝ ተማሪነታቸውን ቀደም ብሎ ከተላኩት የትምህርት ውጤቶች በመረዳት የአንድ ዓመት ጊዜ ጨመረላቸው ። አራት ዓመት ሲሞላ አየር ኃይል እንደጠበቀው አንድ ዲግሪ ብቻ ሳይሆን ሁለተኛውን ዲግሪያቸውን (ማስተር ኦፍ ሳይንስ በማኔጅሜንት ሳይንስ) ጭምር በከፍተኛ ውጤት የዩኒቨርሲቲው የክብር ተማሪ በመሆን አጠናቀው ወደ አገራቸው ተመለሱ ።



ሜ/ጀ ፋንታ በላይ በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ በተለያዩ የኃላፊነት በታዎችና ደረጃዎች ተዘዋውረው የሰሩ ሲሆን በበረራው መስክ በአስተማሪነት ያገለገሉ ከመሆናቸውም በላይ ከአነስተኛ ማስተማሪያና ከፍተኛ የአየር ማጓጓዣ አውሮፕላንና ሚግ-23 አውሮፕላኖችን የበረሩ የአቪዬሽን ሰው ነበሩ ። በአዛዥነትና ሥራ አመራርም አሥመራ የነበረው የሁለተኛው አየር ምድብ ፣ ደብረ ዘይት የሚገኘው የአንደኛው አየር ምድብ አዛዥና ፣ ጠቅላይ መምሪያ ውስጥ የዘመቻ መምሪያ ኃላፊና እንዲሁም በተለያዩ ሌሎች ከፍተኛ የስታፍ መኰንን ኃላፊነት ሥራዎች ተመድበው የሚመሰገን የሥራ ውጤት አሳይተዋል ። በተለይም አየር ኃይሉ በአሰራሩ ዘመናዊ

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንዲሆን በተመደቡባቸው ክፍሎች ሁሉ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሟሉ በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል ፡፡ ለምሳሌ የፋይናንስ ዳሬክተር ሆነው የሂሳብ አያያዙና የደሞዝ ክፍያ ብር እየተቆጠረ እንዳይከፈልና በዘመናዊ የአይቢኤም የሂሳብ መሳሪያ ቼክ እየተዘጋጀ እንዲከፈል በመደረጉ አየር ኃይሉ ወደ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ አንድ እመርታ እንዲያደርግ በማድረግ ዋናው ድርሻ የሳቸው ነው ፡፡ የአየር ኃይል ሰራዊት በበዝባዥ ነጋዴዎች እንዳይበዘበዝ ወታደራዊ መደብር እንዲቋቋም አሰራሩን በማጥናትና ሥራ ላይ በማዋል ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል ፡፡

እ.አ.አ በ 1969/70 ዓም የሶማሊያ ጦር ምስራቅ ኢትዮጵያን እያቋረጠ ወራሪውን በመቀጠል ጂጂጋን በመያዝ አልፎ ድሬዳዋን ለመያዝ እየተቃረበ በሄደበት ጊዜ ይህን አደገኛ ወረራ ለማስቆም ፣ የጠላት ጦር አይቀጡ ቅጣት ተቀጥቶ ብዙ ጉዳት እንዲደርስበትና የተረፈውም ጦር እግሬ አውጪኝ ብሎ በመጣበት ወደ አገሩ እንዲሸሽ በዛል የጦር አመራር በመስጠት ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱት ኰ/ል ፋንታ ነበሩ ፡፡



በሌሊት የተጀመረው የሱማሊያ ጦር ወረራ የመድፍ ጥይት ፍንዳታ በወቅቱ በአካባቢው ከነበረው ከባድ የክረምት ዝናብ ፣ ነጐድጓድና መብረቅ ጋር ያሳስት ስለነበረ ተኩሱ ከጠላት የሚመጣ መሆኑንም እርግጠኛ መሆን አልተቻለም ፡፡ ድሬዳዋ ሆኖ ይሰማ የነበረው የተኩስ ድምፅ ከሩቅ እየቀረበ ሲሄድ ጉዳዩን ለማጣራት በአየር ኃይል ዘመቻ ክፍል በኩል የምድር ጦሩን የቀጠና አዛዦች

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ለመጠየቅ ተሞከረ ። ከነሱ የተገኘው መረጃ ባንድ በኩል የወገን ጦር በልምምድ ላይ ነውና ሊያሳስብ አይገባም የሚል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ እርግጠኛ አይደለንም የሚል ነበር ። በዚህ ባልተረጋገጠ ሁኔታ የተኩስ ድምፅ እየቀረበ በመምጣቱ አሁንም የጦሩን አዛዦች በመጠየቅ እንደገና ለማጣራት ተሞክሮ ተመሳሳይ መልስ ተገኘ ። ለማንኛውም “የልምምድ” ተኩሱ እየገፋ መጥቶ አውሮፕላን ማረፊያው በመድፍ ጥይት ይደበድብ ጀመር ። የሶማሊያ ጦር ግፊት ከፍተኛ ሲዋጋ የነበረው የሚሊሺያ ጦር ሸሸት ጀመረ ። ሽሽቱ ፈጣንና ተመልካችን ግራ የሚያጋባ ስለነበረ በቅርብ ሆነው ይመለከቱ የነበሩት የአየር ኃይል የዘምቻና የግንባሩ አዛዥ ኰ/ል ፋንታ በላይ ያንን ትርምስ ዝም ብለው ማየት አልተቻላቸውም ። የጦሩን አዛዦች ለማግኘት ሙከራ እያደረጉ እስከዚያው ድረስ ጦሩ እንዳይሸሽና የበለጠ የውጊያ ወረዳ እንዳይለቀቅ ለማድረግ መሯሯጥ ጀመሩ ። ይህንን ያለሥጋት ለመስራት እንዲያስችላቸው የአየር ኃይሉ አውሮፕላኖች መሬት ላይ እንዳሉ እንዳይመቱና እናይቃጠሉ ተነቃንቀው ወደ ደብረ ዘይት ሄደው ውጊያውን ከዚያ እየተነሱ እንዲቀጥሉ አደረጉ ። ያገርን ዳር ድንበር የማስከበር ጉዳይ ሆነና የአየር ኃይሉን ዘመቻ የሚመሩት መኰንን በዚያን ዕለት በመሬት የተሰለፈውን ጦርም እንደገና ለማረጋጋትና የመከላከል ተግባሩን እንዲቀጥል ከፍተኛ ትግል ማድረግ ነበረባቸው ። ክላሽንኮባቸውን ወድረው የሚሊሺያ ጦር አባሎችን “የት ነው የምትሄዱት” ? እያሉ እያስቆሙ በመምከር ፣ ያንንም እያደረጉ ወደ ኋላ መሸሽ የፈለጉትን ደግሞ ውጊያውን ካልቀጠሉ ዕርምጃ እንደሚወስዱባቸው እያስፈራሩ ውጊያውን ትቶ ወደ ድሬዳዋ ሲጐርፍ የነበረውን ጦር በማስቆምና የሱማሌን ጦር እንዲቋቋም በማድረግ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል ።

ኰ/ል ፋንታ ይህን በማድረግ ላይ እንዳሉ የወቅቱ የጦርነት ሂደት በፈጠረው ሁኔታ አስገዳጅነት በወጣው ዕቅድ መሰረት ለውጊያው ወሳኝነት ያላቸው ተዋጊና ትራንስፖርት አውሮፕላኖች ፣ እየተነሱ ወደ ደብረ ዘይት እንዲንቀሳቀሱ ተረገ ። ሁኔታው በጣም አስጊ ሆኖ ድሬዳዋ ትያዛለች የሚል ጭንቀት ነበር ። በመሆኑም በወቅቱ የነበሩት የአየር ኃይል አዛዥ ብ/ጀ ታዬ ጥላሁን የድሬዳዋን አየር ጣቢያ ለቆ ለመውጣት አስፈላጊውን ዝግጀት እንዲያደርጉ ለዘመቻ ኃላፊው ለኰ/ል ፋንታ ትዕዛዝ አስተላለፉ ። ይህ ትዕዛዝ አየር ጣቢያው ውስጥ ያለ ማንኛውም ለጠላት ጥቅም ያገለግላል የሚባልን መረጃ የያዘ ፋይል ሁሉ እንዲቃጠል የሚጠይቅ ነበር ። ውጊያው እየተፋፋመ የሶማልያ ጦር ወደ ድሬዳዋ እየተጠጋ ሲሄድ ጀ/ል ታዬ ደጋግመው ስልክ እየደወሉ ጠላት ከመድረሱ በፊት ዶክሜንት አቃጥለው እንዲወጡ ሜ/ጀ ፋንታን አዘዙ ። የአየሩ ሁኔታም እጅግ በጣም መጥፎ ስለነበር ተዋጊ አውሮፕላኖች ከሃረር ሜዳ ተነስተው መመለስና ማጥቃት አልቻሉም ። ይሁን እንጂ የአየር ሁኔታ ከቀኡ አጋማሽ ላይ ስለተሻሻለ ተዋጊ አውሮፕላኖች ከሐረር ሜዳ ተጠርተው በመምጣት ድሬዳዋ አካባቢ ደርሶ የነበረውን የሶማልያ ወራሪ ጦር በመደብደብ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰው የተረፈው በመጣበት እግሩ ወደ አገሩ እንዲፈረጥጥ አድርገው ድሬዳዋ ድናለች ። ልበ ሙሉውና አይበገሬው ፋንታ በላይ ተስፋ ባለመቁረጥ ጦሩን ማስተባበርና ድሬዳዋን መከላከል ቀጠሉ ። የጦር አውሮፕላኖች ከደብረዘይት እየተመላለሱ ድሬዳዋን የመከላከል ውጊያ ቀጠሉ ። ድካሙ የኋላ ኋላ ውጤት ሳያስገኝ አልቀረም ። የሶማልያ ጦር በኢትዮጵያ አፀፋ ማጥቃት

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ብዙ ተጐድቶ የተረፈው በመጣበት እግሩ እየሮጠ ተመለሰ ። ጠላት ድሬዳዋን ይዝ ኖሮ የኢትዮጵያ ጦር ሽሽቱን አዲስ አበባ ድረስ ይቀጥል ነበር ። ባንፃሩ የሶማልያ ጦር ሞራሉ ተገንብቶ በድል አድራጊነት የሶማልያ ፕሬዝዳንት ዚያድ ባሬ እንዳቀደው ወረራው ናዝሬት ድረስ ሊቀጥል ይችል ነበር ። ይህንን ለቀለበሰውና በድል ለተፈፀመው ጦርነት ኰ/ል ፋንታ በላይና በውጊያው የተሳተፉት የአየር ኃይል አባሎች ሁሉ ከፍተኛ ምስጋና ይገባቸዋል ። በምድር ጦር በኩል የአየር መቃወሚያ ባትሪ ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ ጠላትን ለመመከት በተረገው ጥረት ለተገኘው ድል ባለውለታ ነው ።

ሜ/ጀ ፋንታ በላይ የጠላትን ጦር ለመመለስና ድሬዳዋን ለማዳን ለህይወታቸው ሳይሳሱ ላደረጉት ጀግንነት የተሞላበት ከፍተኛ የጦር አመራር ፣ ለኢትዮጵያ ባለውለታ ናቸው ። ለረጅም ጊዜ የማይግባቧቸው የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ፣ ለተረገው አገሪቱ ለማትረሳው ለጀ/ሉ ከፍተኛ ውለታ ዕውቅና የመስጠት በጐ ፈቃድ ባይኖራቸውም በዚያ በአስቸጋሪ ወቅት ድሬዳዋ አካባቢ ላደረጉት ከፍተኛ አስተዋፅዖ በምድር ጦር ጓዶቻቸው ተመስግነውበታል ። የአየር ኃይል ተዋጊዎችም ከደብረዘይት እየተመላለሱ የጠላትን ጦር በማጥቃት እንዲሸነፍ ወደር የሌለው አመራር በመስጠት ያንን ፈታኝና ቀውጢ ቀን በጀግንነት እጅግ በተሳካ ሁኔታ በመወጣታቸው የሥራ ባልደረቦቻቸው አገራቸውና የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያስታውሷቸው ይኖራሉ ።



ሜ/ጀ ፋንታ በፕሬዝዳንት መንግስቱ አመራር ከፍተኛ ቅሬታ የነበራቸው ፣ አገሪቱ ከዓመት ዓመት በማያልቅ ጦርነት ውስጥ ገብታ ኢኰኖሚዋ እየደቀቀ ፣ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ በመድረሱ የአመራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ያስፈልገናል ብለው የሚያምኑ የአገር ተቆርቋሪ ሰው ነበሩ ። የአገር ውስጡ የሰሜን ጦርነት እንዲያበቃ ፣ ሰላማዊ ንግግር እንዲደረግና የሕዝቡ የፖለቲካ ፣ ኢኰኖሚያዊና ማህበራዊ ጥቅሞች እንዲሻሻሉ ፣ በመንግስትና በፓርቲው የተለያዩ መዋቅሮች አማካኝነት የሰፈነው አምባገነናዊነት እንዲለወጥና የሕዝቡ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ ለሙሉ እንዲረጋገጡ ፣ ፍትህና ሰብዓዊ መብቶች ተከብረው የሕዝቡ መጨፍጨፍ ፣ መታሰርና ስደት እንዲቆም ፣ በአገሪቱ የሰፈነው የሶሻሊስት ሥርዓት ወደ ባሰ የኢኰኖሚ ውድቀት ውስጥ የከተተን ስለሆነ መለወጥ አለበት በማለት ከሌሎች ጀ/ል መኰንኖች ጋር በመተባበር ለውጥ ለማምጣት ሞክረው ሳይሳካ በመቅረቱ ሕይወታቸውን ለሚወዷት አገርና ሕዝብ ሰውተዋል ። ጀ/ል ፋንታ አዋቂ ፣ ደፋርና ጀግና ፣ በችሎታቸውና

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

በጠባያቸው ምስጉን ፣ በሰራዊቱ እጅግ ተወዳጅ ፣ አስተዋይና በሳል መኰንን ነበሩ ። ፕሬዝዳንት መንግስቱ ኃይለማርያም ሥራቸውን እንደማይወዱላቸውና አስጊ እንደሆኑ ቀደም ብለው የተረዱት በመሆኑ አደገኛ ነው ብለው ከውትድርናው ዓለም እንዲወጡና የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ተብለው እንዲሾሙ ተደረገ። ታድያ ያም ሆኖ ጀ/ል ፋንታ ከሰራዊቱና ከመሪዎቹ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ሳያቋርጡ በመቆየት የመንግስት ለውጥ ለኢትዮጵያ ትንሳኤ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አምነውበት ፤ የአገር ፍቅር ከሚያቃጥላቸው ሌሎች ጀ/ሎች ጋር መክረው ዘክረው አገሪቱን ከችግር ማጥ ለማውጣት ግትር የሆነው የጦረኝነት አቋም እንዳልሰራና መንግስት የአመራር ስልት መቀየር እንደሚያስፈልገው ለፕሬዝዳንቱና ለሌሎቹ ከፍተኛ ባለሥልጣናት ለማስረዳት ብዙ ሞክረው ሊሳካ ስላልቻለ ኃይል ከመጠቀም ሌላ አማራጭ ጠፍቶ መፈንቅለ መንግስት ታቀደ ። የግንቦት 1981 ዓም ኩዴታ ተሞክሮ ባለመሳካቱ ኢትዮጵያ እኒህን ምስጉን ፣ የምትኩራባቸውን አዋቂ ልጇን ፣ የነበሯትን ምሁርና በየሙያቸው ብዙ ልምድ የነበራቸውን ሌሎች የበሰሉ ከፍተኛ የጦር ጀኔራሎች ፣ በአመራር ላይ በነበሩት ፕሬዝዳንት ለምን ተደፈርኩ ባይነት እንዲረሸኑ ተደረገ ።

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com